በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን፡፡

# አሠርቱ ትእዛዛት - ክፍል ፯

መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

**E-mail:** kesisolomon4@gmail.com

*ቦታ፡-* ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ

በየሳምንቱ ረቡዕ ምሽት ከ12፡30 – 1፡30

**ሚያዝያ ፲፪ ቀን ፳፻፫ ዓ.ም.**

# አሠርቱ ትእዛዛት - ዘጠነኛው ትእዛዝ

- *‹‹አትመኝ።›› __ዘጸ 20፡17፡፣ ዘዳግ 5፡21፡፡__*
- «የባልንጀራህን ቤት አትመኝ የባልንጀራህን ሚስት ሎሌውንም ገረዱንም በሬውንም አህያውንም ከባልንጀራህ ገንዘብ ሁሉ ማናቸውንም አትመኝ።» *__ዘጸ 20፡17፡፡__*

*__ምኞት ምንድር ነው?__*

- የሰው ልጆች በዓይን ያዩትን፣ በእጅ የዳሰሱትን፣ በጆሮ የሰሙትን፣ ልብ የወደደውንና የፈቀደውን ለማግኘት ሲሉ መሻታቸው ነው፡፡ *__ማቴ 5፡17-21፡፡__*
- ምኞት ሦስት ዓይነት ሲሆን እነርሱም መንፈሳዊ፣ ሥጋዊና ሰይጣናዊ በመባል ይታወቃሉ፡፡
- መንፈሳዊ ምኞት የመንፈሳውያን አባቶችና እናቶች ሕይወት አውቆና ተረድቶ እንደነርሱ ለመሆን ስንል የሚገጥሙንን ፈተናዎች እንድንታገስ የሚያደርገን ኃይል ነው፡፡
- ሥጋዊ ምኞት ከፍ ያለ ምድራዊ ሞያ ያላቸውን አይተን ተግተን በመሥራት እንደነርሱ ለመሆን መሻት ሆኖ ሲገኝ ክርስቲያኖች እንዲይዙት ይበረታታሉ፡፡ በምትኩ ሳይሠሩና ሳይደክሙ ቁጭ ብሎ የሌላውን ሀብትና ንብረት የእኔ ባደረገው ብሎ መመኘትና ይህም እውን እንዲሆንልን የኃጢአት መንገዶችን ወይም አማራጮችን መጠቀም የሚወገዝ የሥጋ ምኞት ሆኖ ይተረጎማል፡፡
- ሰይጣናዊ ምኞት በረቂቅ መንገድ ሰይጣን የሚያሳድርብን ምኞት ነው፡፡ አዳምንና ሔዋንን አምላክ መሆንን እንዲመኙ አድርጎ አዋርዶ ጸጋቸውን አስገፍፏል፡፡
- ይህ ትእዛዝ የተሰጠን ምኞት የኃጢአት ሁሉ መነሻ ስለሆነ ነው፡፡ ማመንዘር፣ ሐሰተኛነት፣ መግደል… የሚመነጬት ከምኞት ነው፡፡ ሰው ምኞቱን ማሸነፍ ከቻለ ታላቁን ኃጢአት ድል ያደርገዋል፡፡ ምኞትን የምናሸንፈውም በመሸሽ ነው፡፡

# <u>አሠርቱ ትእዛዛት - ዘጠነኛው ትእዛዝ</u>

- ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለደቀ መዝሙሩ ለጢሞቴዎስ የመከረውም ይህንኑ ነው፡፡ «ከክፉ የጎልማሳነት ምኞት ሽሽ፡፡» ***<u>ካል ጢሞ 2፡22፡፡</u>***
- ምኞት በሰው ልብ ውስጥ ሲያድግ እያሰቡ ወደ መደሰት፣ ለመፈጸም በመጎምዠት እያደገ ሄዶ በተግባር ኃጢአትን እስከመፈጸም ስለሚያደርስ አስቀድሞ መሸሽ ከሁሉ የላቀ መፍትሔ ነው፡፡
- ምኞት የተመኙትን በመፈጸም የሚያበቃ ኃጢአት አይደለም፡፡ ምኞትን ለማሳካት ሲባል ወደ መዋሸት፣ ማታለል፣ መስረቅ፣ መግደል፣ … ሊያድግ ይችላል፡፡ ስለዚህ ወደ ባሰ ሁኔታ ከመግባት አስቀድሞ ከምኞት መሸሽ ያስፈልጋል፡፡

## *<u>ለምኞት የሚያነሳሱ ምክንያቶች</u>*

### <u>ኑሮዬ ይበቃኛል አለማለት</u>

- ውስጣዊ ፍላጎታችንን ያለኝ ይበቃኛል በማለት ካልገዛነው ሁሉን ወደ መመኘት ያደርሳልና እንደ ቅዱስ ጳውሎስ «ኑሮዬ ይበቃኛል ማለትን ተምሬአለሁና።» ***<u>ፊል 4፡11</u>*** ማለትን እንማር፡፡

### <u>ስንፍና</u>

- ለአባታችን አዳም እንደተነገረው ጥረው ግረው ከመኖር ይልቅ እጅና እግርን አጣምረው በመቀመጥ የሌላው ሀብትና ንብረት የእነርሱ እንዲሆን የሚመኙትን የሚመለከት ነው፡፡ ዘፍጥ 3፡17-19፡፡

### <u>ራስን ከሌሎች ጋር ማወዳደርና የሰይጣን ፈተና</u>

- እንደራስ ሳይሆን እንደ ጎረቤት ለመኖር መጣጣርና ሰይጣን ሔዋንን እንዳሳታት በጎሊናችን ውስጥ የሚያሳድረው ምኞት ናቸው፡፡

# <u>አሠርቱ ትእዛዛት - ዘጠነኛው ትእዛዝ</u>

***<u>ምኞት በእርካታችን የሚገታ አይደለም</u>***

- ምኞት አንድ ጊዜ በልብ ውስጥ ከተተከለ እየደጋገሙ የማድረግ ጾርን ያሳድጋል እንጂ በቀላሉ አንድ ጊዜ ስላደረግነው የሚጠፋ አይደለም፡፡
- አዳም በገነት ካሉት ዛፎች ሁሉ መመገቡ አልበቃውም ከተከለከለው ዛፍ ፍሬ መብላት ብቻ ሳይሆን በልቶ አምላክ መሆንን፣ በለ ብዙ እርሻው አክአብ የናቡቴን መሬት ተመኝቶ እስከመግደል ***<u>ቀዳ ነገ 20፡1-ፍም</u>***፣ ሰባት ሚስቶች የነበሩት ዳዊት የአገልጋዩን የኦርዮንን ሚስት ተመኝቶ ኦርዮን እስከማስገደል ***<u>ካል ሳሙ 12፡9</u>***፣ ሰሎሞንም በጥቂቱ በጀመረው የሚበረክቱ ቁባቶችን እስከማስቀመጥ የሚበልጥም ድካም እስከማድረግ አልፈው እስኪሄዱ አድርሶአቸዋል፡፡«ዓይኖቼንም ከፈለጉት ሁሉ አልከለከልኋቸውም ልቤም በድካሜ ሁሉ ደስ ይለው ነበርና ልቤን ከደስታ ሁሉ አላራቅሁትም ከድካሜም ሁሉ ይህ እድል ፈንታዬ ሆነ።» ***<u>መክ 2፡10፡፡</u>***
- «ፈሳሾች ሁሉ ወደ ባሕር ይሄዳሉ፥ ባሕሩ ግን አይሞላም ፈሳሾች ወደሚሄዱበት ስፍራ እንደ ገና ወደዚያ ይመለሳሉ። ነገር ሁሉ ያደክማል ሰው ይናገረው ዘንድ አይችልም ዓይን ከማየት አይጠግብም፥ ጆሮም ከመስማት አይሞላም።» ***<u>መክ 1፡7-8፡፡</u>*** እንዳለ ምኞት ሊረካ የማይችል መሆኑን ነግሮናል፡፡
- ምኞትን ያሸነፉት እንደ ዮሴፍ የሸሹት እንጂ ተጋፍጠው የበደሉት አይደሉምና የሚሻለው መሸሽ ነው፡፡ ***<u>ዘፍጥ 39፡1-23፡፡</u>***

# <u>አሠርቱ ትእዛዛት - ዘጠነኛው ትእዛዝ</u>

## <u>*የምኞት ዓይነቶች*</u>

- የዓይን አምሮት፣ የሥጋ ፍላጎት፣ የገንዘብ መሻት የምኞት ዓይነቶች ናቸው፡፡ «ዓለምን ወይም በዓለም ያሉትን አትውደዱ፤ በዓለም ያለው ሁሉ እርሱም የሥጋ ምኞትና የዓይን አምሮት ስለ ገንዘብም መመካት ከዓለም ስለ ሆነ እንጂ ከአባት ስላልሆነ፥ ማንም ዓለምን ቢወድ የአባት ፍቅር በእርሱ ውስጥ የለም።» <u>***ቀዳ ዮሐ 2፡16፡፡***</u>
- ቅዱስ ጳውሎስ «ሥጋ በመንፈስ ላይ መንፈስም በሥጋ ላይ ይመኛል፡፡» <u>***ገላ 5፡17፡፡***</u> በማለት ምኞት ከፈቃዳችን ውጪ የሚመነጭ መሆኑን ጽፎልናል፡፡ «የክርስቶስ ኢየሱስም የሆኑቱ ሥጋን ከክፉ መሻቱና ከምኞቱ ጋር ሰቀሉ።» ገላ 5፡24 ምኞትን እንዴት ልናሸንፈው እንደምንችል ገልፆልናል፡፡
- ኤሳውን ብኩርናውን በምስር ወጥ እንዲሸጥ ያደረገው፣ እስራኤላውያንንም በእግዚአብሔር ላይ ለማጉረምረም ና በመጨረሻም ለመቀሰፍ ያበቃቸው የመብል ምኞት ነው፡፡ <u>***ዘፍጥ 25፡29-34 እና ዘኁ 11፡1-34፡፡***</u>
- የገንዘብ፣ የንብረት፣ የክብር ወይም የታዋቂነት፣ የሥልጣንና የማዕረግ፣ የውበት ምኞቶችም እንዲሁ ናቸው፡፡ ስለዚህም አምላካችን «የባልንጀራህን ቤት አትመኝ» በማለት አዘዘን፡፡
- ምኞት ሰይጣን «ወደ ሰምይ ዐርጋለሁ፥ ዙፋኔንም ከእግዚአብሔር ከዋክብት በላይ ከፍ ከፍ አደርጋለሁ፥ በሰሜንም ዳርቻ በመሰብሰቢያ ተራራ ላይ እቀመጣለሁ ከዳመናዎች ከፍታ በላይ ዐርጋለሁ፥ በልዑልም እመሰላለሁ፡፡» <u>***ኢሳ 14፡13-14፡፡***</u> ብሎ ወደ ጥልቁ የወደቀበትና አዳምንና ሔዋንንም ያሳተበት ዘወትር የሰው ልጆችንም የሚያሰናክልበት በነፍሳችንም እንደንሞት የሚዋጋበት ጾር ነው፡፡ ጌታችን «እርሱ በመጀመሪያ ነፍሰ ገዳይ ነበር፡፡» ዮሐ 8፡44 እንዳለን፡፡
- ስለዚህ ሁሉ ከንቱ መሆኑንና ዓለሙም ምኞቱም የሚያልፉ መሆኑን በመገንዘብ ስለ ሌሎች ሰዎች በማሰብ፣ የሰውን ወገን ሁሉ በማፍቀርና በቸርነት በመርፋት ከምኞት በመሸሽ እንኑር፡፡ <u>***መክ 1፡14፤ ቀዳ ዮሐ 2፡17፡፡***</u>

# <u>አሠርቱ ትእዛዛት - አሥረኛው ትእዛዝ</u>

- *‹‹ባልንጀራህን እንደራስህ ውደድ።›› <u>**ዘሌ 19፡18፡፡**</u>*
- «ነገር ግን ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ እኔ እግዚአብሔር ነኝ።» ***<u>ዘሌ 19፡18፡፡</u>***
- ባልንጀራህን ውደድ የተባለው በሥላሴ አርአያ የተፈጠረውን ሰው በሰውነቱ መውደድ እንደሚገባ ለማመልከት ነው፡፡ «ባልንጀራህን ውደድ ጠላትህንም ጥላ እንደ ተባለ ሰምታችኋል። እኔ ግን እላችኋለሁ፥ በሰማያት ላለ አባታችሁ ልጆች ትሆኑ ዘንድ ጠላቶቻችሁን ውደዱ፥ የሚረግሙአችሁንም መርቁ፥ ለሚጠሉአችሁም መልካም አድርጉ፥ ስለሚያሳድዱአችሁም ጸልዩ፤ እርሱ በክፎዎችና በበጎዎች ላይ ፀሐይን ያወጣልና፥ በጻድቃንና በኃጢአተኞችም ላይ ዝናቡን ያዘንባልና። የሚወዱአችሁን ብትወዱ ምን ዋጋ አላችሁ? ቀራጮችስ ያንኑ ያደርጉ የለምን? ወንድሞቻችሁንም ብቻ እጅ ብትነሡ ምን ብልጫ ታደርጋላችሁ? አሕዛብስ ያንኑ ያደርጉ የለምን? እንግዲህ የሰማዩ አባታችሁ ፍጹም እንደ ሆነ እናንተ ፍጹማን ሁኑ።» ***<u>ማቴ 5፡42-48፡፡</u>***
- ጌታችን ትእዛዛትን ዘርዝሮ ባስረዳበት ክፍል «ባልንጀራህን እንደራስህ ውደድ፡፡» ብሎአል፡፡ ማቴ 19፡19፡፡
- ባልንጀራን መውደድ ለሰው መልካም ***<u>ሉቃ 10፡25-37</u>***፣ ነፍሱ የምትድንበትን ***<u>ያዕ 2፡8-9</u>*** ማድረግን ያካትታል፡፡
- ባልንጀራንም መውደድ ለራስ የሚሹትን መልካም ነገር ለባልንጀራ ማድረግ ማለት ነው፡፡ «እንግዲህ ሰዎች ሊያደርጉላችሁ የምትወዱትን ሁሉ እናንተ ደግሞ እንዲሁ አድርጉላቸው፤ ሕግም ነቢያትም ይህ ነውና።» ***<u>ማቴ 7፡12፡፡</u>***
- ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንደ ነገረንም ባልንጀራን መውደድ ከራስ ጥቅምም የባልንጀራን ጥቅም መመልከትንም የተመለከተ ነው፡፡ «እያንዳንዱ የባልንጀራውን ጥቅም እንጂ አንድስ እንኳ የራሱን ጥቅም አይፈልግ፡፡» ***<u>ቀዳ ቆሮ 10፡24፣ ፊል 2፡2-4፡፡</u>***

# አሠርቱ ትእዛዛት - አሥረኛው ትእዛዝ

- ባልንጀራውን የሚወድ ሰው ሰውነቱን በዝሙት፣ ሀብቱን በስርቆት፣ ስሙን በሐሰት በማጥፋት ወይም በሐሰት በመመስከር ባልንጀራው የሚጠፋበትን አያደርግም፡፡
- ቅዱስ ጳውሎስ «የትእዛዝ ፍጻሜ ግን ከንጹሕ ልብና ከበጎ ሕሊና ግብዝነትም ከሌለበት እምነት የሚወጣ ፍቅር ነው፡፡» ***1ኛ ጢሞ 1፡5፡፡*** እንዳለን፡፡
- ጌታችን «… ሁለተኛይቱም። ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ የምትል እርስዋን የምትመስል ይህች ናት። ከእነዚህ የምትበልጥ ሌላ ትእዛዝ የለችም።… በፍጹም ልብ በፍጹም አእምሮም በፍጹም ነፍስም በፍጹም ኃይልም እርሱን መውደድ፥ ባልንጀራንም እንደ ራስ መውደድ በሙሉ ከሚቃጠል መሥዋዕትና ከሌላው መሥዋዕት ሁሉ የሚበልጥ ነው አለው።» ***ማር 12፡31-33፡፡***
- እግዚአብሔርን መውደድና ባልንጀራን መውደድ አይነጣጠሉም፡፡ «እግዚአብሔርን ስንወድ ትእዛዛቱንም ስናደርግ የእግዚአብሔርን ልጆች እንድንወድ በዚህ እናውቃለን። ትእዛዛቱን ልንጠብቅ የእግዚአብሔር ፍቅር ይህ ነውና፤ ትእዛዛቱም ከባዶች አይደሉም።» ***1ኛ ዮሐ 5፡2-3፡፡***
- «እኛ ወንድሞችን የምንወድ ስለ ሆንን ከሞት ወደ ሕይወት እንደ ተሻገርን እናውቃለን፤ ወንድሙን የማይወድ በሞት ይኖራል። ወንድሙን የሚጠላ ሁሉ ነፍሰ ገዳይ ነው፥ ነፍሰ ገዳይም የሆነ ሁሉ የዘላለም ሕይወት በእርሱ እንዳይኖር ታውቃላችሁ። እርሱ ስለ እኛ ነፍሱን አሳልፎ ሰጥቶአልና በዚህ ፍቅርን አውቀናል፤ እኛም ስለ ወንድሞቻችን ነፍሳችንን አሳልፈን እንድንሰጥ ይገባናል። ነገር ግን የዚህ ዓለም ገንዘብ ያለው፥ ወንድሙም የሚያስፈልገው ሲያጣ አይቶ ያልራራለት ማንንም ቢሆን፥ የእግዚአብሔር ፍቅር በእርሱ እንዴት ይኖራል? ልጆቼ ሆይ፥ በሥራና በእውነት እንጂ በቃልና በአንደበት አንዋደድ።» ***1ኛ ዮ ሐ 3፡14-18፡፡***

# <u>አሠርቱ ትእዛዛት - አሥረኛው ትእዛዝ</u>

- «በብርሃን አለሁ የሚል ወንድሙንም የሚጠላ እስከ አሁን በጨለማ አለ። ወንድሙንም የሚወድ በብርሃን ይኖራል ማሰናከያም የለበትም፤ ወንድሙን የሚጠላ ግን በጨለማ አለ፥ በጨለማም ይመላለሳል፥ የሚሄድበትንም አያውቅም፥ ጨለማው ዓይኖቹን አሳውሮታልና።» ***<u>ቀዳ ዮሐ 2፡9-11፡፡</u>***
- እግዚአብሔርንና ባልንጀራን መውደድ የሕግ ሁሉ ፍጻሜ ነው፡፡
- «ማንም። እግዚአብሔርን እወዳለሁ እያለ ወንድሙን ቢጠላ ሐሰተኛ ነው፤ ያየውን ወንድሙን የማይወድ ያላየውን እግዚአብሔርን ሊወደው እንዴት ይችላል? እግዚአብሔርንም የሚወድ ወንድሙን ደግሞ እንዲወድ ይህች ትእዛዝ ከእርሱ አለችን።» ***<u>ቀዳ ዮሐ 4፡20-21፡፡</u>*** እንደተባልነው እንደራሳችን ባልንጀሮቻችንን እንድንወድ ይገባል፡፡
- «ሕግ ሁሉ በአንድ ቃል ይፈጸማልና፥ እርሱም፦ ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ የሚል ነው።» ***<u>ገላ 5፡14፡፡</u>***
- «ለወገኔ ይጠቅማል በማለት ወይም በከንቱ ውዳሴ ምክንያት አንድ እንኳ አታድርጉ፥ ነገር ግን እያንዳንዱ ባልንጀራው ከራሱ ይልቅ እንዲሻል በትሕትና ይቍጠር፤ እያንዳንዱ ለራሱ የሚጠቅመውን አይመልከት፥ ለባልንጀራው ደግሞ እንጂ።» ***<u>ፊል 2፡3-4፡፡</u>***
- «አባትህንና እናትህን አክብር፥ ባልንጀራህንም እንደ ራስህ ውደድ አለው።» ***<u>ማቴ 19፡19፡፡</u>***
- «ሁለተኛይቱም ይህችን ትመስላለች፥ እርስዋም፦ ባልንጀራህን እንደ ነፍስህ ውደድ የምትለው ናት።» ***<u>ማቴ 22፡39፡፡</u>***
- «ሁላችሁም በባልንጀራችሁ ላይ ክፉን ነገር በልባችሁ አታስቡ ፡፡» ***<u>ዘካ 8፡17፡፡</u>***

For your queries or questions E-mail:
kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf :
www.zeorthodox.org

# ወስብሐት ለእግዚአብሔር፡፡